# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

**ከህዳር 27- ታህሳስ 4፤2017 ዓ.ም**
**DEC 6-13, 2024 G.C**

## 1.ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ባለ ልዩ መለያ ኮድ ያለው ደረሰኝ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እንዲያሳትሙ ማሳሰበያ ተሰጠ

*December 8, 2024*

ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ባለ ልዩ መለያ (QR Code) ያለው ደረሰኝ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ማሳተም እንዲጀምሩ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ማሳሰቢያ ሰጠ፡፡

ማሳሰቢያው የተሰጠው ኅዳር 24 ቀን 2017 ዓ.ም. ሚኒስቴሩ ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች የደረሰኝ ኅትመትን በተመለከተ በጻፈው ደብዳቤ ነው፡፡

ባለልዩ መለያ ያለው ደረሰኝ የማተም ፈቃድ የተሰጠው የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት መሆኑን የሚገልጸው ደብዳቤው፣ ግብር ከፋዮች ደረሰኙን በተባለው ጊዜ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል ከታኅሳስ 1 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ የኅትመት ጥያቄ በማቅረብ ማሳተም እንዲጀምሩ አሳስቧል፡፡

ኅዳር 3 ቀን 2017 ዓ.ም. የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመርያን ለማሻሻል በወጣው መመርያ 188/2017 መሠረት፣ ደረሰኝ ሲታተም ልዩ መለያ ኮድ ታክሎበት መሆን እንዳለበት መገለጹ ይታወሳል፡፡

ማንኛውም ታክስ ከፋይ ያሳተመውን ደረሰኝ መጠቀም የሚችለው፣ የማሻሻያ መመርያው ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ባለው ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ መሆኑን ተገልጾ ነበር፡፡

በዚህ መሠረት ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ከታኅሳስ ጀምሮ ደረሰኝ ማሳተም እንዲጀምሩ ሚኒስቴሩ ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/136183/

## 2. የፋይናንስ ዘርፍ የሰው ኃይል ክፍተቶችን ለመቅረፍ የክህሎት ምክር ቤት እንዲቋቋም ምክረ ሐሳብ ቀረበ

**December 8, 2024**

የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል እጥረት እንዳለበት የሚነገርለት የፋይናንስ ዘርፍ፣ ክፍተቶቹ እንዲቀረፉ የሚያግዝ የክህሎት ምክር ቤት ሊቋቋም እንደሚገባ ምክረ ሐሳብ ቀረበ፡፡

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ምንም እንኳን በንፅፅር የተሻለ የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዳለው ቢታመንም ከዘመኑ ጋር የዋጀ የላቀ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት እንዳለበት፣ በዘርፉ ዕድገት ላይ የሚያተኩር የምርምር፣ የማማከርና የሥልጠና ተቋም ክፍተት እንዳለም ይነገራል፡፡ በቴክኖሎጂ፣ በፈጠራ፣ በመረጃ ትንተና፣ እንዲሁም በሥልጠናና በማማከር አገልግሎቶች የሚታወቀው ዓለም አቀፉ ተቋም ስካይኩዌስት (SKYQUEST) ማኔጂንግ ዳይሬክተር አካሽ ብሃቭዛር ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ ለውጭ ተዋንያን ክፍት ሊሆን በዝግጅት የሚገኘው የባንክ ዘርፍ በተለይም ከሰው ኃይል ጋር በተያያዘ በአጭር ጊዜ ሊከናወኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ ከሌሎች አገሮች ከሚገኙ ባንኮች ምርጥ ተሞክሮ መውሰድ ዋነኛው ነው፡፡

በተለይ የአገር ውስጥ ባንኮች አንድ ላይ በመሆን የክህሎት ምክር ቤት ሊያቋቁሙ እንደሚገባ የተናገሩት ብሃቭዘር፣ የተወዳዳሪነት ክፍተቶች (Competency Gaps) መጠኑ ይለያይ እንጂ በሁሉም ባንኮች ላይ የሚስተዋሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች ስለሆኑ ነው ብለዋል፡፡

በቅድሚያ ባንኮቹ ስለጉዳዩ ያላቸው ክፍተት ከተለየ በኋላ ክፍተቱን ለማስተካከል ምክር ቤቱ ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑን፣ ይህንን ለማድረግ አስፈላጊው ነገር ቁርጠኝነት መሆኑን ኤክስፐርቱ አስረድተዋል፡፡

በዚህ ወቅት በተለይም ባንኮችን ጨምሮ በፋይናንስ ዘርፉ ያለው ክፍተት የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሳይሆን ለመገልገልና ለመጠቀም ያለ ቁርጠኝነት እንደሆኑ የተናገሩት ባለሙያው፣ ይህንን ቅርፅ ማስያዝ የሚያስችል አቀራረብና ዘዴ መጠቀም የግድ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ባንኮች በተለይም በውጭ ንግድ የተሰማሩ ደንበኞቻቸው ዕቃዎችን ከሚገዙባቸው አገሮች ባንኮች ጋር ትስስር በመፍጠር መሥራት ከቻሉ ከአገልግሎት ቅልጥፍና ባሻገር፣ ቀጣይ የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ለውድድር ዝግጁ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያስችላቸው እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/136185/

## 3. የላኪውንና ተቀባዩን የጥራት ደረጃ ማሟላት – ወቅቱ የሚጠይቀው መስፈርት

**December 11, 2024**

በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ጥራት ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለዚህም ዓለም የደረሰባቸውን የጥራት መስፈርቶች እና የጥራት መለኪያ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን የተቀባዩም ሆነ የላኪውን ሀገር የጥራት ደረጃ ማሟላት ያስፈልጋል።

በዚህ ሂደትም የምርቶችና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃ ብቻ አይደለም መፈተሽ ያለበት፤ የጥራት መለኪያ ላቦራቶሪዎችና መሳሪያዎች በየጊዜው በትክክል ስለመሥራታቸው መፈተሽ እንዳለባቸውም የዘርፉ ባለሙያዎች ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

ኢትዮጵያም በቅርቡ ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ያሟላ የጥራት መንደር አስመርቃለች። ሀገሪቱ መንደሩ በተመረቀበት ማግስት ባሳለፍነው ሳምንት "የጥራት መስፈርቶችን ከማሟላት ወደ ላቀ የአፈፃፀም ብቃት!" በሚል መሪ ቃል የዓለም የጥራት ቀንንም አክብራለች።

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር መዓዛ አበራ እንደገለፁት፤ የዘንድሮው የዓለም የጥራት ቀን መሪ ቃል ፅንሰ-ሃሳብ በዓለም ዙሪያ ላሉ አምራቾች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የደረጃ መሥፈርቶችን ከማሟላት አልፈው ወደ ላቀ የአፈጻጸም ብቃት የመሻገርን አስፈላጊነት ማስገንዘብ ነው።

https://press.et/?p=142766

## 4. በኢትዮጵያ የክልል የኢኮኖሚ አካውንት መመሪያ ይፋ ሆነ

**ኢዜአ፡ ታህሣሥ 3/2017**

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው የክልል የኢኮኖሚ አካውንት መመሪያን ይፋ አደረገ።

የክልል የኢኮኖሚ አካውንት የከተማ አስተዳደሮችንና የክልሎችን ኢኮኖሚያዊ አፈጻጸም ለመለካት የሚያስችል እንደሆነ ተገልጿል።

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የሁሉም ክልሎችና የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ፕላንና ልማት ቢሮ ሃላፊዎች በተገኙበት በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የክልል ኢኮኖሚ አካውንት የአሰራር ዘዴ መመሪያ በቢሾፍቱ በተካሄደ መድረክ ላይ ይፋ አድርጓል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ በረከት ፍስሀፂዮን በዚሁ ጊዜ እንደገለፁት፤ የክልል የኢኮኖሚ አካውንት የክልሎችን ኢኮኖሚያዊ አፈጻጸም ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው።

ኢትዮጵያ በ1953 ዓ.ም ብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ተግባራዊ ማድረግ የጀመረች ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ የክልል የኢኮኖሚ አካውንት እንዳልነበራት ገልጸዋል።

ከተማ አስተዳደሮችና ክልሎች ከዚህ ቀደም የኢኮኖሚ ሁኔታቸውን ለመለካት ወጥ ያልሆነ እና ከብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ጋር ያልተናበበ ስርዓትን ይከተሉ እንደነበር አውስተዋል።

ይህም በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን አዳጋች አድርጎት መቆየቱን ገልፀዋል።

ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከዚህ በመነሳት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮችና የሁሉም ክልሎች ፕላንና ልማት ቢሮዎች እንዲሁም ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የክልል የኢኮኖሚ አካውንት የአሰራር ዘዴ መመሪያን ሲያዘጋጅ መቆየቱን ገልጸዋል።

መመሪያ በአሁኑ ወቅት የተጠናቀቀ መሆኑን ጠቁመው፤ በዛሬው ዕለት ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ይፋ መደረጉን ገልጸዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5615836

**5. Efforts Will Continue to Gain Momentum in Ethiopia's Coffee Production as Major Producing Nation: PM Abiy**

**ENA: December 11/2024**

Prime Minister Abiy Ahmed noted that Efforts to position Ethiopia as not just the origin of coffee but a major coffee-producing nation continue to gain momentum.

Over the past five years, annual coffee production has doubled from 500,000 tons. In the 2016 fiscal year, the coffee trade generated over 1.4 billion US dollars in revenue, the Prime Minister shared through his social media channels.

This year, the goal is to increase this figure to 2 billion USD, with significant progress already being made, he indicated.

According to the Premier, modern coffee irrigation systems and machine-assisted harvesting, achieving yields of up to 60 quintals per hectare, are clear indicators of this success.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5606211

**6. Prime Minister Abiy Says Ethiopia's Gold Mining Industry Presenting Immense Potential for Local, International Investment**

**ENA: December 10/2024**

Prime Minister Abiy Ahmed revealed that Ethiopia's gold mining industry stands out as a significant driver of growth, presenting immense potential for both local and international investment.

"Ethiopia is one of the fastest-growing economies in Africa and a beacon of opportunity on the continent. Among its many thriving sectors, the gold mining industry stands out as a significant driver of growth, presenting immense potential for both local and international investment," the premier wrote on X.

The Shakiso and broader Guji regions, rich in gold deposits, are prime locations for mining activities, he pointed out.

According to the Prime Minister, a notable recent development is the inauguration of YMG Gold Mining, which brings promising opportunities for the local community in Shakiso.

Employing advanced mining technology that operates entirely on gravity, YMG's processes are both innovative and environmentally friendly, as they avoid the use of harmful chemicals, Abiy said.

The PM added that: "During my visit to Guji, I also had the opportunity to observe the activities of Midroc Gold, one of Ethiopia's leading gold mining companies.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5601102

**7. Ethiopia Anticipated to Become Regional Leader in Cotton Production**

**ENA: December 13/2024**

The immense potential of Ethiopia in cotton production would position the country a regional leader in the sector, Chairperson of Eastern and Southern Africa Cotton Organization (ESACO), Driana Lwandar emarked. A two-day regional workshop on harnessing opportunities and inclusive dialogue for sustainable cotton and textiles sector transformation is taking place in Addis Ababa. In his opening remarks, Ethiopia's Agriculture State Minister Meles Mekonnen emphasized the importance of the workshop in fostering sustainable economic growth through the cotton and textiles sector.

The state minister highlighted that the ministry has recognized the importance of enhancing production and productivity of cotton.

To this effect, various measures are put in place to achieve the objectives of import substitution and export promotion to generate foreign currency, ensuring industrial input and structural transformation while securing high level of employment opportunities, he added.

Explaining the untapped potential of the cotton and textile sector with ample land and water resources, suitable agro-climatic conditions and productive workforce, Meles stressed the government's commitment to transforming its economy, particularly through cotton and textile production.

With 3 million hectares of land suitable for cotton cultivation, the country has the potential to produce over 3 million tons of cotton annually— sufficient for both domestic needs and export, he added.

https://www.ena.et/web/eng/economy

**8. Nurturing cooperatives to contribute for macro-economic development**

**ENA: December 13, 2024**

Cooperatives have a good potential to contribute to the recently introduced macro-economic reform and improving the welfare of communities. The Addis Ababa Cooperatives Commission recently organised a consultative forum between cooperatives and unions, which aimed at enhancing market linkage between producers and traders. In this case cooperatives are said to be the right prototypes to realize the link and insure the planned macro- economic reform and national development.

"When the Country was facing scarcity of products and exceeding price of commodities and service, cooperatives have shown great commitment in delivering quality products with fair price" said Lilti Giday, Commissioner of the Addis Ababa Cooperatives Commission.

She noted that they have been playing crucial role in assisting the government with its heavy burdens of controlling rising illegal price limits and inflation.

https://press.et/herald/?p=107386